**በለንደንም የዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ መልዕክተኞች ከሀገራችን ሕዝብ ጋር ያለንን ወገንተኛነት በጥቅም ልታስለውጡንና ልትከፋፍሉን አትችሉም እንበላቸው!**

# <u>የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪ</u>

ላለፉት ሃያ ዓመታት፡

- የአንድ ድርጅት ዘረኛና ከፋፋይ የአገዛዝ ፖሊሲውን ጭኖ፣ ኢትዮጵያዊው የአንድነት ትስስራችንን እንደ ነቀዝ እየበላ፣ በሀገራችንና በሕዝባችን ህልውና ላይ ሌት ከቀን እየሰራ ያለው፣
- የመላውን ሕዝብ ተሳትፎ ሙሉ ለሙሉ ባገደ ዓለም አቀፍ ደባ የኢትዮጵያን አካል አስቆርሶና የባህር መውጫ አልባ አድርጎ ሥልጣን ላይ በመቆናጠጥ፣ አሁንም ከምዕራቡ የሀገራችን ክፍል መሬት እንደ ዳቦ ለሱዳን እየገመሰ በመስጠት ላይ የሚገኘው፣
- በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ የሀገራችንን ገበሬዎች በግድ አፈናቀሎ፣ መላው ቤተሰባቸውን የትም እየበተነ፣ የትምና መቼም ተደርጎ በማያውቅ ዋጋ ለአንድ ሄክታር ካንድ ፓውንድ ያነሰ ክፍያ በመቀበል ለአረብና ለህንድ አራሾች መሬታችንን እየቸበቸበ ያለው፣
- የሀገር አንድነትና ዴሞክራሲያዊ መብት ይከበር ያሉ የሕዝብ ልጆችን እያደነ በጠራራ ፀሐይ የሚያርደው፣ እያፈነ ደብዛቸውን የሚያጠፋው፣ ከ40 ሺህ በላይ የፖለቲካ እስረኞችን በሚታውቁም፣ በማይታወቁትም የድብቅ እስር ቤቶች አስሮ የሚገኘው፣
- ብዛት ያላቸውንና የሚያሰጉትን የፖለቲካ ድርጅቶች በሀገራቸው ውስጥ በግልጽ የመንቀሳቀስ መብት የነፈገው፣ እራሱ ባዘጋጀው ህግ ስር ለመስራት የሚሞክሩትንም እራሱ የደነገገውን ሕግ እየጣሰ፣ በእመቃና በአፈና መከራ የሚያሳየው፣
- የሀገራችንን ኢኮኖሚ፣ የሥልጣን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችና ሌሎችንም ዋና ዋና ጉዳዮች ከአንድ አካባቢ በተወለዱ አልጠግብ ባይ መንደርተኞች እጅ እያግበሰበሰ የሚገኘው፣
- የሀገራችንን ህዝብ በነፃ የመደራጀት መብት በአልባኒያዊ የአምባገነንነት ሥልቱ ሙሉ ለሙሉ ጨፍልቆ፣ በስንት የሙያ ማህበራት መሪዎች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ጋዜጠኞችና ንፁሃን ዜጎች ደም እጆቹ ተጨማልቆና አሁንም እየተጨማለቁ ያለው፣
- የሕዝባችንን መረጃ በነፃ ማግኘት መብት ጨፍልቆ፣ በሀገራችን ሊበቅል የሞከረውን ገለልተኛ የህዝብ መገናኛ በአፈናና እመቃ በትኑ ያጠፋው፣ አሁንም ከውጭ በኢትዮጵያዊያን ወገኖች የሚተላለፉ ለምሳሌ ፍኖተ-ዴሞክራሲ ሬዲዮና ኢሳት ቴሌቭዥን፣ በባዕዳን መንግሥታት የሚተዳደሩትንም ለምሳሌ የአሜሪካ ድምጽና የጀርመን ድምፅ ሬዲዮኖች ለማፈን በሙሉ ሃይሉ እየሰራ ያለው፣

በአጠቃላይ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት ተፀንሶ፣ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት አድጎ፣ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት የአገዛዝ መንበር ላይ ወጥቶ፣ ሀገርና ህዝብ አጥፊ ፖሊሲውን ነድፎ አገዛዙን በማራመድ ላይ ያለው ወያኔ፣ ስደተኛውን በውሸት ፕሮፓጋንዳው ለማማመልና ለመከፋፈል በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ሎሌ መልዕክተኞቹን ልኮ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ዋና ዓላማውም በኢንቬስትሜንት፡ በመኖሪያ ቤት ግንባታ እና በሌሎች የውሸት ጥቅማ ጥቅሞች በማባበል በአገር ቤት በወገኑ ላይ ለሚደርሰዉ ሰቆቃ ደንታ ቢስ ለማድረግ ነው። በዘርና በጎሳም ከፋፍሎ የሚገጥመዉን ተቃዉሞ ለማስወገድ ጭምር። ወያኔ በትዕቢትና በድፍረት ይህን ለማድረግ ማሰቡ በራሱ ጅልነት ነዉ። የወያኔ የጥቅም ተካፋዮች የሆኑና በጠባብ የዘረኝነት ገመድ የተተበተቡ ደካሞች ብቻ ለዚህ ዓይን ላወጣ ወንጀል ከጎኑ ሊሰለፉ ይችሉ እንደሆን እንጂ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ስደተኛ በነፃ አገር ዉስጥ እየኖረ በአገሩ ጉዳይ ነፃነቱን በገዛ እጁ አሳልፎ ይሰጣል የሚል እምነት የለንም። በዉጭ የምንገኘው ኢትዮጵያዊያን፣ ሕዝባችን በትግሉ ድል ሲያደርግና የሀገርና የሥልጣን ባለቤትነቱን ሲያረጋግጥ፣ በሀገራችን በነፃነት የመኖርና ሀብትም ሆነ ንብረት የማፍራት መብታችን እንደሚረጋገጥ ጠንቅቀን እናውቃለን።

ስለሆነም ማንኛዉም ለሃገሩና ለወገኑ ተቆርቋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ እነዚህ የአገርና የወገን ፍቅርና ብሄራዊ ስሜት የሌላቸዉ የወያኔ ሎሌዎችና ግብረ አበሮቻቸዉ በጠሩት ዝግጅት ላይ እንዳይገኝና በወገኖቹ ደም ከተጨማለቁ ጋር አብሮ እንዳይቆም፡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለጊዜያዊ ጥቅም እንዳይንበረከክና በገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶቻቸው ተሳታፊ እንዳይሆን እንጠይቃለን። በአንድነት በመሆን እነዚህን የአገር አንድነትና የወገን ጠላቶችን በፅኑ ለመቃወም በተዘጋጀው ሰልፍ ላይ እንዲገኝም ለመላው የለንደንና አካባቢው ኗሪ ኢትዮጵያዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ስፍራዉ፡ *Imperial College, London, Sherfield Bldg., South Kensington Campus, Exhibition Road, London, SW7 2AZ* ቀንና ሰዓት፡ *16 April, 2011 2:00pm - 7:00pm*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘረኝነትን በትግሉ ያስወግዳል! የኢትዮጵያ አንድነት ለዘላለም ይኑር!*

የተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያን ስብስብ በለንደን